የሰ/መ/ቁ. 54567

የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች ፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት - ዓ/ህግ መቅጫ ለገሠ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ - ነ/ፈጅ ኃይለእየሱስ ደምሴ - ቀረቡ፡፡

2. ሮማን ገብሩ - የቀረበ የለም፡፡

3. ማሩ አላምረው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በፍትሐብሔር ክርክር ሂደት በፍርድ ቤት የታገደ ንብረት እግዱ ተግባራዊ በሆነበት ጊዜ ተሸጦ ሲገኝ እግዱን ያሰጠውና የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ስላለው መፍትሔ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ ሲሆን የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በአመልካች ጠያቂነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተደረጉ ናቸው፡፡ የስር ከሳሽ የክስ ይዘትም አቶ ብርሃኑ ታርቆ የተባሉ ግለሰብ በከሳሽ ድርጅት በቋሚ ሰራተኛነት ተቀጥረው ከ1988 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመዘንጋትና አጋጣሚውን በመጠቀም ብር 28,794.70 /ሃያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰባ ሳንቲም/ በማጉደላቸውና ለግል ጥቅም በማዋላቸው ይህንን ገንዘብ እንዲከፍሉ ለምዕራብ ጎጃም መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ በመመስረት የመ/ቁጥር 2312 ተከፍቶ ተከሳሽ አቶ ብርሃኑ ታርቆ ተጠርተውና በጉዳዩ ላይ ተከራክረው የግራ ቀኙን ክርክር የመረመረው ፍርድ ቤት መጋቢት 08 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቶ ብርሃኑ ታርቆን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ዋናውን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለዱና ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ውሣኔ መስጠቱን፣ ለዚህ ፍርድ ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ የአቶ ብርሃኑ ታርቆን ቤት የፍርድ ባለመብት የሆነው ድርጅት በዋናው ክርክር ጊዜ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሰጥቶ ለባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የእግድ ትዕዛዙን ያደረሰ ቢሆንም እግዱ ተጥሶ ቤቱን የፍርድ ባለዕዳው ሸጦ መገኘቱን ገልጾ ማዘጋጃ ቤቱ የፍርዱን ገንዘብ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም በቤቱ ላይ እግድ መሰጠቱን ሳይክድ ሁኔታው የተከሰተው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን ገልጾ መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት እንደሌለበት፣ ሰራተኞቹም ወደ

ክርክሩ እንዲገቡለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በአሁኑ አመልካች ጥያቄ መነሻነት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተደርጐ ባቀረቡት መከራከሪያ ለጉዳዩ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በሁዋላ የአሁኑን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ለ1ኛ ተጠሪ የፍርዱን ገንዘብ ያህል እንዲከፍል በማለት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን ግን በነፃ በማሰናበት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ጥፋቱ ሰራተኛ የሆኑት የ2ኛ እና የ3ኛ ተጠሪዎች ሁኖ እያለ መስሪያ ቤት የሆነው አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ መባሉ ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ኃላፊነት አለበት ቢባል ደግሞ የኃላፊነት መጠኑ ሊሆን ይገባ የነበረው ቤቱ የተሸጠበት የገንዘብ መጠን እንጂ 1ኛ ተጠሪ በፍርድ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ እንዲከፈለው የተወሰነውን መጠን ያህል ሊሆን አይገባም የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ ይክፈል ተብሎ የመወሰኑ ሁኔታ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው የጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ የሚፈልገው የገንዘብ መጠን በፍርድ የተረጋገጠ ሲሆን በዋናው ክርክር ጊዜ ደግሞ የአቶ ብርሃኑ ታርቆ ንብረት የሆነውን ቤት በፍርድ ቤት በማስከበር የእግዱን ትዕዛዝ ለአሁኑ አመልካች አድርሶ ባለበት ሁኔታ የቤቱ ባለቤትና የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ግለሰብ ቤቱን ለሌላ ሰው ራሳቸው ሸጠው በመገኘታቸው 1ኛ ተጠሪ ፍርዱን ሊያስፈጽም የሚችለውን የአቶ ብርሃኑ ታርቆን ንብረት ሊያገኝ ያልቻለ መሆኑን፣ እንዲሁም የቤቱ ሽያጭን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ክርክር 1ኛ ተጠሪ አቅርቦም እስከ መጨረሻው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ የአሁኑ አመልካች ሃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረውም እግዱ ለመስሪያ ቤቱ መድረሱን በመካድ ሳይሆን ተግባሩ የተፈፀመው ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጥፋት ነው በማለት መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ያደረገው የእግድ ትዕዛዙ ደርሶት እያለ ይህንኑ ጥሶ ቤቱ እንዲሸጥ አድርጐአል፣ የሰራተኞች ጥፋት ስለመኖሩም አላስረዳም በሚል ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ አጥብቆ የሚከራከረው ጥፋቱ በሰራተኞች የተፈፀመ እንጂ በመስሪያ ቤቱ የተፈፀመ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የአመልካች ሰራተኛ በሆኑት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የተፈፀመ ጥፋት ስለመኖሩ አመልካች ያላስረዳ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይህ ድምዳሜ የማስረጃውን ታዓማኒነት መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን ደግሞ ይህ ችሎት ሊመረምር የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የእግድ ጥሰት ተግባር የተፈፀመው በሰራተኞች ጥፋት መሆኑን አመልካች ካላስረዳ ደግሞ ራሱ ሃላፊነት የማይወስድበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም

የፍርድ ቤት እግድ ትዕዛዝ አለማክበር በሕግ ላይ በትክክል ተገልጾ የተደነገገውን ልዩ ደንብና ሥርዓት መጣስ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2028፣2035 እና 2126 መሠረት ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ነውና፡፡ በመሆኑም አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን ከሕጉ ጋር ያገናዘበ እንጂ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የካሳ መጠኑን በተመለከተ ሲሆን በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ኃላፊነት መጠኑ ሊሆን የሚገባው ቤቱ በእርግጠኝነት የተሸጠበት ዋጋ እንጂ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከአቶ ብርሃኑ ታርቆ ላይ የሚፈልገው የፍርድ ገንዘብ መጠን አይደለም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቤቱ በጨረታ ሳይሆን ከዚህ ውጪ የተሸጠ በመሆኑ በትክክል በምን ያህል ዋጋ እንደተሸጠ ተረጋግጧል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ ቤቱ የተሸጠው በገበያ ዋጋ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች የኃላፊነት መጠኑን የሚቃወምበት ሕጋዊ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡